# የቃላት ጨዋታ

ሃሌታ! ሃሌታ! ሃሌታ!
በቃላት ጨዋታ
ኣንደበት ይፈታ።
የሚገጥም ይገጥማል
ብሎ ግጥም፣ ግጥም!
ለጆሮም ይጥማል፣
ቃል-ኪዳን ፍጥምጥም...
ያልገጠመ ኣይገጥምም
ካለዚያም ኣይጥምም።
ቃላቱ፣ ስንኙ፣
ከሓዲው፣ ኣማኙ፣
ድኩላም ከኣዳኙ፣
ጥንዚዛው፣ ትንኙ
ከልብ ሲገናኙ...
ማን ይሆናል ሞኙ? ማን ይሆናል ሞኙ?
በፍዴል ኣሰካክ፣
በቁመት ኣለካክ፣
በምትክ ኣተካክ፣
በሊጡ ኣቦካክ...
የድኩላው ቅልጥም
ሰብሮ፣ በልቶ፣ ግጥም
የጨው፣ የውሃው ጥም
ካለ ጠጅ ኣይቆርጥም!
ኣይጠ-መጐጥም
ተንበርክኮ ፍርጥም
ሄዶ ላዩ ጥምጥም
ከባሕሩ ስጥም!
ኣንድምታ! ኣንድምታ! ኣንድምታ!
የጠፈሩ ዋልታ
ደድሆና ክትክታ
ሥራ-ፈት ኣውታታ
ምስጢሩን ሲፈታ
ሲያታልል፣ ሲያምታታ...
ሃሌታ! ሃሌታ! ሃሌታ!
በሓዘን፣ ደስታ፣
በጩኸት፣ እሩምታ፣
በለቅሶ፣ በዋይታ፣
በዘፈን፣ በእስክስታ፣
መለከት፣ እምብልታ፣
በቃላት ጨዋታ
ኣንደበት ይፈታ!

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**